## “ስለ እኛ የሚማደው ክርስቶስ ኢየሱስ” -ምን ማለት ነው?

(መድሎተ ጽድቅ ከተሰኘው መጽሀፍ የተቀነጨበ)

ምልጃን በተመለከተ ስለ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡-

" እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን **መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል**፤...እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ **ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና**።" ሮሜ 8፡26-27

ስለ እግዚአብሔር አብም እንዲህ ተብሏል፡-

"እንግዲህ እግዚአብሔር **በእኛ እንደሚማልድ** ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ....." 2 ቆሮ. 5፡20

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ እንዲህ ተብሏል፡ -

"እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፣ የሚኰንንስ ማን ነው? የሞተው፣ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፣ ደግሞ **ስለ እኛ የሚማልደው** ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።" ሮሜ 8፡33-34

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፣ እግዚአብሔር አብም፣ እግዚአብሔር ወልድም ሁሉም የሚማልዱ ከሆነ ምልጃ ማለት ምን ማለት ሊሆን ነው? አንዳቸው የሚማልዱት ወደ ማን ነው? በቅድስት ሥላሴ አካላት መካከል የፈቃድ ልዩነት አለን? እንደዚያ ካልሆነ ለምን እንደዚህ ተባለ? ስለዚህ ነገሩ እንዲሁ በገጸ ንባቡ ታፍሶ የሚቃም ሳይሆን ጥንቃቄ የሚያሻው ጠንካራ የሆነ ቃል ነው ማለት ነው! በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ትምህርት በአእምሮ ሕፃናት የሆኑ ሰዎች የሚጋቱት ወተት ብቻ ሳይሆን ከዚያ ያለፈ የእውቀት ብስለት ያላቸው ጠንካራ ምግብ መመገብ የለመዱ ሰዎች ብቻ ሊመገቧቸው የሚችሉ ጠንካራ ነገሮችም አሉና። መጽሐፍ ቅዱስን ገጸ ንባቡን ማንበብ የቻለ ሁሉ ሐሳቡንም እረዳዋለሁ ማለት የማይችል ስለመሆኑ፣ ቅዱስ ጳውሎስ ገጸ ንባቡን ይዘው የዚያ ፍጻሜ የሆነውን የክርስቶስን ማዳን ግን ለመረዳት ዐቀበት ለሆነባቸው ለአይሁድ ከአሪቱ ሊቀ ካህናትና ከመልከ ጼዴቅ አንጻር እየተረጎመ የተወሰነ ካስረዳቸው በኋላ እንዲህ አላቸው፡-

> ስለ እርሱም የምንናገረው ብዙ ነገር አለን፣ ጆሮቻችሁም ስለ ፈዘዙ በቃል ልንተረጕመው ጭንቅ ነው። ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፣ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም፡፡ ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤ ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው። ዕብ. 7፡11-14

ዕብራውያን በዕድሜ ሳይሆን በእውቀት ሕፃናት ሆነው በመገኘታቸው በጌታችን ሊቀ ካህናትነትና አዳኝነት ሊጠቀሙበት ሲገባቸው እንደ ተሰናከሉበት፣ ዛሬም በማስተዋልና በጥንቃቄ ልንረዳቸው የሚገቡ የእግዚአብሔር ቃላትን እንዲሁ በዘፈቀደ

እየጠቀሱ የሚሰናከሉና የሚጠፉ ወገኖች መኖራቸው አሳዛኝ ነገር ነው። “የማያምኑ ስለ ሆኑ በቃሉ ይሰናከሉበታልና” የተባሉት እንደነዚህ ያሉት ናቸው። 1 ጴጥ.2፡8 ታዲያ “**ስለ እኛ የሚማልደው** ክርስቶስ ኢየሱስ ነው” ማለት ምን ማለት ነው?

ይህን ሐሳብ ከመሠረቱ ለመረዳት ትንሽ ወደ ኋላ መሄድና የሮሜ መልእክትን መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳብ መረዳት የግድ ያስፈልጋል። በሮሜ መልእክቱ ላይ ቅዱስ ጳውሎስ በጥበባቸውና በኃይላቸው ሲመኩ የነበሩ አሕዛብ ሮማውያንና ግሪካውያንም ሆኑ በሕገ ኦሪታቸው ሲመኩ የነበሩ አይሁድ ሁለቱም በሚመኩበት ነገር ያልተጠቀሙበት መሆናቸውን ከምዕራፍ 1 እስከ 3 ላይ በጥልቀት አብራርቶ ካስረዳ በኋላ፣ ሁሉንም የሚያድናቸው የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ መሆኑን እንዲህ ሲል ገለጸ፡-

> ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና፣ የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ፡፡ እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፣ **…** ሮሜ 3፡23-25

በመቀጠልም ይህን እንዲያው በጸጋው የተሰጠውን የመዳን ጸጋ ገንዘብ ለማድረግ ምን ማድረግ እንደሚገባ በምዕራፍ 6 ላይ በጥምቀት ከክርስቶስ ከሞቱና ከትንሣኤው ጋር መሳተፍ የግድ አስፈላጊ መሆኑን ገለጸ። በመቀጠልም በክርስቶስ ጸጋ የዳኑ ሁሉ የክርስቶስ አካል በሆነው በዚህ የከበረ ሰውነታቸውና ብልቶቻቸው ከኃጢአት መራቅና መጠበቅ፣ መልካም ሥራ በመሥራት መልካም ፍሬ ማፍራት በጸጋው የዳኑ ሰዎች ክርስቶሳዊ ግዴታ መሆኑን በስፋት አብራርቶ አስረዳ። ከዚያ በመቀጠል ደግሞ በጸጋው የዳኑ ሰዎች ከክርስቶስ ክብር ለመሳተፍ የሚችሉት እንዴት እንደሆነ እንዲህ አለ፡-

> አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን፡ ሮሜ 8፡17

ስለዚህ በጸጋው መዳን ማለት ከክብሩ ለመሳተፍ ከመከራውም መሳተፍን የግድ የሚል ነገር ነው ማለት ነው። ነገር ግን እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ አለ፤ እርሱም እኛ ከመከራው ለመሳተፍ ዓቅምና ችሎታ አለን ወይ? በፈተናው ብንወድቅስ ከክብሩ ተለይተን ልንቀር ነው ወይ? ፈተናውን ማለፍ አቅቶን ወድቀን ላለመቅረታችን ዋስትናችን ምንድን ነው? የሚል መሠረታዊ ጥያቄ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ከዚያው ቀጥሎ የገለጻቸው ነገሮች ለዚህ መጽናኛና ማበረታቻ የሚሆኑንን፣ ብሎም ዋስትና የሚሰጡ ነገሮችን ነው። እነዚህ ምንድን ናቸው?

1ኛ) ከመከራው በኋላ የሚገኘው ክብር አሁን ከምንቀበለው መከራ ጋር የማይመጣጠን ልዩና ታላቅ መሆኑ - ቁጥር 18 ላይ “ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ” ብሎ የገለጸው ሐሳብ ማለት ነው።

2ኛ) ይህ ሊገለጥ ያለው ክብር የክብሩ ተሳታፊና ባለቤት የሆነው ሰው ብቻ ሳይሆን ከክብሩ በቀጥታ የማይሳተፉት ሌሎች ፍጥረታት እንኳ የሚናፍቁት መሆኑ “የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና። ….ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው። ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና። …” ሮሜ 8፥19-25 ይህም ማለት የክብሩ ቀጥተኛ ተሳታፊ

ያልሆኑት ሌሎች ፍጥረታት እንኳ ይህን ያህል የሚጓጉለትና በናፍቆት የሚጠብቁት ከሆነ የክብሩ ቀጥተኛ ወራሾች የሆንነው እኛማ ምን ያህል ወደ ክብራችን የሚወስደውን መከራ ልንታገሠውና ልንወደው ይገባን ይሆን? እንደ ማለት ነው።

3ኛ) መንፈስ ቅዱስ ድካማችን የሚያግዘንና አብሮን የሚሠራ መሆኑ

> እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፣ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና። ሮሜ 8፡ 26-27

ይህም ማለት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በድካማችን ጊዜ የሚያበረታን፣ በፈተናው ውስጥ ከመጀመሪያው ጀምሮ የሚመራንና በክፉ ፈቃዳትና በርኩሳት መናፍስት ላይ ድል ማድረግን የሚሰጠን እርሱ መሆኑን ለመግለጽ ነው። እኛ በፈተና ጊዜ እንዴት ማድረግ እንዳለብን ግራ እንጋባለንና። ያን ጊዜ ለራሳችን ብቻ የሚተወን ከሆነ በፈተናው በቀላሉ እንሸነፋለን፣ ተስፋም እንቆርጣለን። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ከልጆቹ ስለማይለይ አስቀድሞ ፈተናውን በተለያየ መንገድ ውስጣችን እንዲረዳው በማድረግ ያዘጋጀናል። ወደ ጦርነቱ ስንገባም እርሱው ራሱ ስለ እኛ ይዋጋልናል። እርሱ በእኛ ውስጥ ተዋግቶ ድል በማድረግ መልሶ የድል አድራጊነት ክብር ይሰጠናል። እንዲህ ሲያደርግ ግን እኛን ከጨዋታ ውጭ አድርጎ ሳይሆን በፈተናው ሂደት ውስጥ አብሮን በመሥራት ነው።

እኛ የሚጠቅመንን ካለማወቃችን የተነሣ ፈተናው እንዲርቅልን ስንጸልይ የሚጠቅመን መሆኑን የሚያውቀው እርሱ፣ ቅዱስ ጳውሎስን “ጸጋዬ ይበቃሃል፣ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ” እንዳለው ያደርግልናል። 2 ቆሮ. 12፡9 ሰማዕታትን አነሣስቶ ወደ ደም ጻድቃንን ወደ ገዳም፣ አጠቃላይ ክርስቲያኖችን ወደ መልካም ገድል ትሩፋት

ያነሣሣቸዋል። በሂደቱም ይረዳቸዋል፣ ቢወድቁ በውስጣቸው ነውና እንዲጸጸቱና ንስሐ እንዲገቡ ይቀሰቅሳቸዋል። ንስሐ ሲገቡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ሲቀበሉ ኃጢአታቸውን ይቅር ይላቸዋል። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ስለሆነ ከክርስቶስ ከመከራው መሳተፍን ልንፈራ አይገባም ማለቱ ነው ብፁዕ ጳውሎስ።

4ኛ) “እግዚአብሔርንምለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።” ሮሜ 8፡ 28 ሌላው መጽናኛችን ደግሞ ይህ ነው። ምንም ነገር ቢመጣብን፣ እግዚአብሔር እንዲያ እንዲሆን የሚፈቅደው ለእኛ ጥቅም ብቻ ነው። ስለዚህ ይህን የመሰለ ማንኛውንም ነገር ሁሉ ለእኛ በጎ በሚሆን ሁኔታ የሚያደርግና የሚቆጣጠር ሁሉን ቻይ የሆነ አባት ስላለን በምንም ሁኔታ ከክርስቶስ መከራ መሳተፍን ልንፈራና ልንሰቀቅ አይገባም ማለቱ ነው።

5ኛ) እግዚአብሔር በእኛ ላይ ዳኛችን ብቻ ሳይሆን አባታችንም፣ ጠበቃችንም፣ ልክ እርሱ ራሱ እኛን እንደ ሆነ ሆኖ የሚያየን ነው። ከቁጥር 31 ጀምሮ የሚያብራራው ሐሳብ ይህን ነው:-

> እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም? እግዚአብሔር የመረጣቸውን

ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው? የሞተው፣ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፣ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ሮሜ 8፡31-34

ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እስከሆነ ድረስ፣ አንድያ ልጁን ስለ እኛ አሳልፎ እስከ መስጠት ደርሶ የወደደን እስከሆነ ድረስ፣ የሚያጸድቀውና የሚኮንነው (የሚፈርደው) እርሱ ራሱ እግዚአብሔር እስከሆነ ድረስ፣ ዲያብሎስ ከሚያመጣው ፈተና እና በእግዚአብሔር ዘንድ ከሚያቀርበው ክስ የተነሣ አንፈራም ማለቱ ነው ብፁዕና ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ። ሰይጣን እኛን በእግዚአብሔር ፊት ሊከስ ቢሞክር፣ ጌታችን የእኛ ዳኛ ብቻ ሳይሆን ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ የዋጀንና የገዛን ውድ ልጆቹና አካሎቹ ስለሆንን የሰይጣንን ክስ ውድቅ ያደርግበታል እንጂ ለመፍረድ የሚቀመጥ ፈራጅ ብቻ ሳይሆን ልጆቹ፣ አካላቶቹ በመሆናችን የእኛ ክስ አይቀበለውም ማለቱ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደ ዳኛ የእኛን ጉዳይ ለመፍረድ የሚቀመጥ ፈራጅ ብቻ ሳይሆን ልጆቹ፣ አካላቶቹ በመሆናችን የእኛ ክስ የእርሱም ክስ ነው፣ ስለዚህ ዳኛችን ብቻ ሳይሆን እንደ ጠበቃ ስለ እኛ ከሳችንን ውድቅ ለማድረግ ማንኛውንም ነገር የሚጠቀም ነው።

“የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው” አለ። ይህም ማለት ዳኛው እርሱ እኛን ጻድቃን ያለን ከሆነ፣ ያውም እግዚአብሔርን የመሰለ ዳኛ እንዲህ ያለን ከሆነ፣ ከሳሹን ማን ይሰማዋል? ስለዚህ ፈተናዎችን መፍራትም ሆነ የሰይጣንን ክስ መፍራት የለብንም። ስለ እኛ ራሱን አሳልፎ የሰጠ ሲሆን፣ በዚህም በቃኝ ሳይል አሁንም ስለ እኛ የሚያስብ፣ የዲያብሎስን ክስ ውድቅ እያደረገ የክብር አክሊል የሚያቀዳጀን ይህን የመሰለ አባት እያለን ፈተናንና የሰይጣንን ክስ መፍራት አይገባንም ማለቱ ነው።

ስለሆነም በቆረሰው ሥጋው ባፈሰሰው ደሙ አምነን በጥምቀት ልጆቹ ሆነን ሥጋውንና ደሙን በልተን አካላቱ የሆንነውን እኛን፣ ከዚያ በኋላም ከእርሱ ጋር አብረን ስንሠራ በመንገድ ላይ በሚገጥሙን በተለያዩ ድቀቶች ንስሐ ገብተን የኃጢአታችን ማስተሥረያ የሆነውን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የተቀበልን እኛን እንደ ባዕድ ሰው እንዲሁ ዝም ብሎ አሳልፎ አይሰጠንም። እኛ እርሱን ስለሆንን ዲያብሎስን ያሳፍረዋል እንጂ አይሰማውም። ስለዚህም በዓቅማችን ከክርስቶስ መከራ በምንሳተፈው ሱታፌ በሚገጥሙን ነገሮች ወድቀን ዲያብሎስ ከስሶ ከክርስቶስ ከክብሩ ከመሳተፍ ውጭ እንሆናለን ብላችሁ አትፍሩ፤ ምክንያቱም ይህ ሁሉ ሕያው የሆነ ማጽናኛና ማበረታቻ አለንና ማለቱ ነው።

ስለዚህ ይህ ቃል ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስ ስለ እኛ ያለውን ታላቅ የሆነ የቅርብ ጥበቃና ልዩ እንክብካቤ ለመግለጽ የተጠቀመበት ልዩ አገላለጽ ነው። የክርስቶስን ጽንዐ ፍቅር፣ የአባትነቱን የቸርነት ስፋት ወሰን የለሽነት የገለጸበት ግሩምና ድንቅ ቃል ነው። ስለዚህ ይህን የመሰለ በእግዚአብሔር ዘንድ መታመናችንን እጅግ ከፍ የሚያደርግ ድንቅ ቃል መሰናከያ መሆን የለበትም። ሰይጣን ለአዳምና ለሔዋን ለሕይወት የተሰጣቸውን ቃል ለመፈተኛ እንዳደረገባቸው እኛም በዚህ ድንቅ የሆነ ቃል በዲያብሎስ ማደሪያዎች መፈተኛችን መሆን የለበትም። ይህን ቃል ከዲያብሎስ ምርኮ ማስመለስ ይገባናል። ልንደሰትበትና ልንጽናናበት የሚገባ ድንቅ የእግዚአብሔር ቃል ነውና።

ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ ቀጥሎ እንዲህ አለ፡-

ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፣ ወይስ ጭንቀት፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ራብ፣ ወይስ ራቁትነት፣ ወይስ ፍርሃት፣ ወይስ ሰይፍ ነውን? . . በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። ሞት ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣

መላእክትም ቢሆኑ፣ ግዛትም ቢሆን፣ ያለውም ቢሆን፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ ኃይላትም ቢሆኑ፣ ከፍታም ቢሆን፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ፡፡

ሐዋርያው ይህን በመሰለ ድፍረትና ተአምኖ በሙሉ ልብ እንዲናገር ያደረገው ይህ ሁሉ ተስፋ ነው። ሮሜ 8፡35-39

ስለሆነም ሮሜ 8፡34 እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ልዩ ፍቅርና ጥበቃ የሚገልጽ ዕንቁ የሆነ የተስፋና የአምላካዊ ኃይል ቃል ነው እንጂ ያልታደሉ ሰዎች እንደሚሉት ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ስለ እኛ እግዚአብሔር አብን “ማርልኝ ይቅር በልልኝ" እያለ ይማልዳል ማለት አይደለም። ሐሳቡ ፈጽሞ ከዚህ የራቀ ነው። ስለሆነም ሮሜ 8፡34 እንደየ ዓቅማችን ከክርስቶስ ከመከራው በመሳተፍ ከክብሩም ለመሳተፍ እንችል ዘንድ የሰይጣንን ከሳሽነት እንዳንፈራና እንዳንሳቀቅ ኃይልና ብርታት የሚሰጥ ድንቅ ቃል እንጂ መናፍቃን እንደሚያጣምሙት ባለ ሁኔታ የምንሳቀቀው ቃል አይደለም።

በኦሪት ዘዳግም ላይ “ከተማይቱን ለመውሰድ በመውጋት ብዙ ቀን ከብበህ ባስጨነቅሃት ጊዜ፣ ምሳርህን አንሥተህ ዛፎቿን አትቍረጥ፤ ከእነርሱ ትበላለህና አትቍረጣቸው” ተብሎ የተገለጸው መናፍቃን ለራሳቸው የተሳሳተ አረዳድ ተገዢ ሊያደርጉት እስኪማርኩት የደረሱ የእግዚአብሔር ቃል ብታይ ቃሉን ልቁረጠው ልፋቀው አትበል ማለቱ ነው። ዘዳ. 20፡19 “ከእነርሱ ትበላለህና አትቍረጣቸው” የተባሉት በውስጣቸው ልዩ ጣዕም ያለው ምግብ ይዘው ሳለ መናፍቃን መራራ አስመስለው የሚሳዩዋቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎች ሲገጥሙህ እነዚህን ላጥፋቸው ወይም ልፋቃቸው አትበል፤ ምክንያቱም “ከእነርሱ ትበላለህና አትቍረጣቸው።” ሮሜ 8፡34ም እንደዚሁ በውስጡ የምንበላው ሕያው ምግብ የያዘ ዛፍ ስለሆነ መቁረጥ ሳይሆን አላዋቂ መናፍቃን ያበላሹትን የተሳሳተ አረዳድ አራግፎ በመጣል መመገብና ጣፋጭነቱን ማጣጣም ይገባል። እንደዚያ ማድረግ እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን።

## ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ሮሜ 8:34ን ምን ብሎ ተረጎመው?

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ይህን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል የተረጎመው እንደዚህ ነው፡-

“ስለ እኛ የሞተው፣ ከሙታንም የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፣ ስለ እኛ የሚማልደው እርሱ ክርስቶስ ነው” አለ። አሁን ያለው በቀደመ ክብሩ (በእግዚአብሔር ቀኝ ቢሆንም እንኳ ስለ እኛ ማሰብን፣ ለእኛ የሚያስፈልገውን ማድረግን አልተወም፣ አላቋረጠምና። ስለ እኛ መሞት ብቻ ከዚህ በኋላ ይበቃኛል፣ ከእንግዲህ ወዲያስ በቃኝ አላሰኘውምና። አንድ ሰው እርሱ የሚቻለውን ማደረጉ ብቻ ሳይሆን ሌላውን ስለዚያ ሰው መጠየቁም የታላቅ ፍቅር መገለጫ ነውና። “ስለ እኛ ይማልዳል” ሲል ሊገልጽ የፈለገው (የሚገልጸው) ሐሳብ ይህ ነውና። እንዲህ በሰዎች ልማድ እና ወደ ታች ዝቅ ወዳለ ደረጃ ወርዶ እስከ መግለጽ የደረሰው ክርስቶስ ለእኛ ያለውን ፍቅር ለማስረዳት ነው።

“ለገዛ ልጁ ያልራራለት” የሚሉትን ቃላትም እንደዚሁ ባለ ሁኔታ የማንረዳቸውና የማንወስዳቸው ከሆነ እጅግ በጣም ብዙ ስህተቶች ላይ እንወድቃለንና። ለመግለጽ የፈለገው ዓላማው ይህ ማለትም የክርስቶስ ፍቅር መሆኑን ትረዳ ዘንድ መጀመሪያ “በእግዚአብሔር ቀኝ አለ” ካለ በኋላ ቀጥሎ “ስለ እኛ የሚማልደው" አለ። ይህም የአብና የወልድን የክብራቸውን

አንድነትና እኩልነት ካሳየ በኋላ፣ ለእኛ የሚያደርገው መግቦት የማነስ አለመሆኑን ለማስረዳት “ስለ እኛ የሚማልደው” አለ። እርሱ ራሱ ሕይወት ነውና! የመልካም ነገሮች ሁሉ መገኛ ምንጭ ነውና! ከአብ ጋር በሁሉ ነገር እኩል ነውና! ሙታንን ለማንሣትም ቢሆን፣ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ለማድረግ እኩል ከሃሊ ነውና! (ዮሐ.5፡ 19:21:36)

<u>**ታዲያ እንዲህ ከአብ ጋር በከሃሊነትና በሥልጣን አንድ የሆነ እርሱ እኛን ለመርዳት ማላጅ መሆን እንዴት ያስፈልገዋል? እንዴት እርሱ አማላጅ ይሆናል? እንዴት ይማልዳል ይባላል?**</u> የተፈረደባቸውንና የተኮነኑትን ነጻ ያወጣቸውና ያዳናቸው እርሱ፣ ከሞት ፍርድና ከኩነኔ ነጻ ያወጣና ያዳነ እርሱ፣ ጻድቃንና ልጆች ያደረጋቸው እና እጅግ ከፍ ወዳለ ክብር ያወጣቸው እርሱ፣ ይህን ሁሉ ከፈጸመና ካከናወነ በኋላ፣ ባሕርያችንን በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ ካስቀመጠው በኋላ፣ በጣም ቀላል ስለሆኑት ነገሮች ማላጅ መሆን እንዴት ያስፈልገዋል? ሲያልን በሥልጣኑ የበዘበዘ፣ ሞትን በኃይሉ የሻረ፣ ልጅነትንና ትንሣኤን የሰጠ፣ ባሕርያችንን ከራሱ ባሕርይ ጋር አዋሕዶ በሰማያት በንጉሡ ዙፋን ላይ ያስቀመጠው እርሱ፣ ስለ ጥቃቅን ነገሮች ለምን ለማኝ ማላጅ ይሆናል?

**ስለዚህ ምልጃን የጠቀሰበት ምክንያት እርሱ ለእኛ ያለውን የፍቅሩን ጥልቀትና ብርታት ፍቅሩ እስከ ምን ድረስ የሚዘልቅ ወሰን የለሽ መሆኑን ለመግለጽ እንጂ ሌላ ምክንያት እንዳልሆነ ተረዳ።** አብም ሰዎች ከእርሱ ጋር ይታረቁ ዘንድ እንደሚማልድ ሆኖ ለእኛ ተገልጾልናልና፤ “እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን" ተብሏልና። 2 ቆሮ. 5፡20 እንግዲህ እግዚአብሔር ቢማልድም፣ ሰዎች ደግሞ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ቢሆኑም፣ በዚህ አገላለጽ ምክንያት ለእግዚአብሔር ክብር ተገቢ ባልሆነ መንገድ ልንረዳው አይገባንም። ሆኖም ከዚህ ሁሉ ለእኛ ከተነገረን የምንሰበስበው አንድ መሠረታዊ ነገር ብቻ ነው፤ እርሱም እርሱ **ለእኛ ያለውን የፍቅሩን ጽናትና ጥልቅነት ነው**። መንፈስ ቅዱስም ስለ እኛ በማይነገር መቃተት የሚማልድልን ከሆነ፣ ክርስቶስም ስለ እኛ የሞተልንና የሚማልድልን ከሆነ፣ አብም ስለ አንተ አንድ ልጁን ያልራራለት ከሆነ፣ እና የመረጠህና ያጸደቀህ ከሆነ፣ ታዲያ ምን የምትፈራው ነገር አለህ? ወይስ ይህን በመሰለ ልዩና ገናና የአባት ፍቅር ውስጥ እየዋኘህ ያለህ አንተ፣ ይህን ያህል ትኩረትና ዋጋ የተሰጠህ አንተ፣ የሚያስፈራህ ምን ነገር ይኖራል ይሆን?

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ መልእክተ ሮሜ

## “መካከለኛ”

አንድ እግዚአብሔር አለና፣ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፣ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ 1 ጢሞ. 2፡5

ኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛ ተብሏል፣ ነውም። መካከለኛ የተባለበት ምክንያትም፣

1. ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው የሆነው እርሱ ብቻ ነውና። እንደ አምላክነቱ ፍጹም እግዚአብሔር እንደ ሰውነቱ ፍጹም ሰው ስለሆነ እግዚአብሔርነትም ሰውነትም ገንዘቡ የሆነ እርሱ ብቻ ነውና። ስለዚህ በተገባ ነገር መካከለኛ ነው። ከእርሱ በቀር ሌላ መካከለኛ የለንም።

2. ሐዲስ ኪዳንን የሠራውና የፈጸመው እርሱ ነውና። ከብሉይ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን ያሸጋገረን እርሱ ስለሆነ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ላይ ይህን ደጋግሞ ገልጾታል። ዕብ. 9፡15፣ 12፡24
3. ሌላው "አንድ መካከለኛ አለ" ብሎ የጻፈበት ምክንያት ደግሞ ግኖስቲኮች የተባሉት መናፍቃን ከእውነተኛው አምላክ ወደዚህ ዓለም የተላኩ ብዙ (30) ኤዎኖች ወይም መካከለኛዎች አሉ ብለው ያስተምሩ ስለነበር፣ መካከለኛው እነርሱ እንደሚሉት የክፉው አምላክ ተቃራኒ ነው ከሚሉት "ደግ አምላክ" ሳይሆን ከአንዱና ብቸኛው አምላክ ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን፣ ያ መካከለኛም 30 ሳይሆኑ አንድ ብቻ የሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለማስረዳት ነው።

ሆኖም ኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛ ነው ማለት ግን ከአብ ያነሰ፣ ሥልጣኑና ክሂሉ በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል የሆነ ማለት አይደለም። ይህ የክህደት ሸለቆ ነው። መካከለኛ ያሰኘው ከላይ እንደተገለጸው በባሕርዩ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑ ነው። ስለዚህ መካከለኛ ማለት አማላጅ ማለት አይደለም፥፤ ፈጽሞ አይገናኝም።

## "የቅዱሳን አማላጅነት ትምህርት የኢየሱስ ክርስቶስን መካከለኛነት ይቃወማል፣ ይጋፋል"

የቅዱሳን አማላጅነት በኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ መካከለኛነት ቦታ ላይ ፍጡራንን ማስቀመጥ ነው ይላሉ። ሆኖም ይህ ጥያቄ ወይም ሐሳብ የተለመደው የፕሮቴስታንቶች ነገሮችን በየፈርጃቸው ያለመረዳት ችግር ውጤት ነው። የቅዱሳን ምልጃ ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛነት ጋር የሚጋጭ አይደለም። ለምሳሌ በራእይ 5 እና 8 ላይ ሰማያውያን መላእክት በምድር ላይ ያሉ የሰው ልጆችን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሲያቀርቡ እናያለን። በራእ. 8፡3-4 "ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ" ይላል። ይህ ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛነት ጋር የሚነጻጸር ነገር አይደለም።

ስለዚህ የኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛነት እና የቅዱሳን ምልጃ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አንዳችን ስለ ሌላችን እንድንጸልይ ያዘዘን እርሱ ነው። እንዲሁም "ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽምግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት" ያለው ቅዱስ መጽሐፍ ነው። ያዕ 5፡14-15 ዳግመኛም ቅዱሳን መላእክትን "ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት" አድርጎ የሰጠን እርሱ ራሱ ነው። ዕብ. 1፡14 ስለሆነም የቅዱሳን ምልጃም የኢየሱስ ክርስቶስን ብቸኛ መካከለኛነት የሚቃወም አይደለም። ይህ ዓይነቱ ስህተት የሚመጣበት አንዱ ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስን ለምን መካከለኛ ብሎ እንደ ገለጸው ጥንተ ምክንያቱን አለመረዳት ነው።

## ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ

## መድሎተ ጽድቅ ቅጽ ፫ (ገጽ 221-235)